# አድራለሁ ቆሜ!

ለቤት ልጅ ስሟን ሲያወጡ
ተማክረው፣ በውል፣ በቅጡ
አስበው፣ አሰላስለው
አውርደው፣ አወራርደው፤
“በሌሊት፣ ታይቶኝ በሕልሜ
ስምሽም፤ “አድራለሁ ቆሜ!”
ይሆናል! ሲሉ አወጡላት፤
አዲስ ልብስም መረቁላት።
“ስጠራሽ፤ ‘አድራለሁ ቆሜ’
መልሺ፤ ‘ለጌታዬ ዕደሜ!’
አደራሽን ልጃችን
ዘወትር እንዲያ እንዲሆን!”



ብለዋት የቤት ልጅ ሆና
ችላ ያን ሁሉ ገበና
ሲጠሯት፤ “አድራለሁ ቆሜ-”
ስትመልስ፤ “ለጌታዬ ዕደሜ!”
ለዓቅመ-አዳም ደረሰችና
ያለ ቄስ፣ ያለ ዲያቆን
አጋቧት ሰጠኝ መርቆን።
ለሰርጉም ሙክት አርደው
ቤተ-ሰቡንም ጠርተው
ጭፈራ፣ ዳንኪራ ዋሉ
ጌቶቹም እራት ሲበሉ
ሙሽራው ሰጠኝ መርቆ
አብርቶ፣ ዳሱን አድምቆ
ኩራዙን ይዞ እንደ ቆመ
ራሱን እንደ ጠመጠመ
ውሏል እንደ ታመመ፣
አጋፋሪና አሰላፊ
ለሁሉም እርሱ ሓላፊ፣
ራሱ ነው ሞሰብ አቅራቢ
ሰርገኛን እጅ አሳጣቢ፣
ማለዳ ዕንጬት ሲፈልጥ
ውጋትም የሚቀስጥ፣
ደረቱን ሲወጋጋው
ወገቡን ማን ይገመው?
ዋግምቱ እስኪገኝለት
አንድም ሰው አላዘነለት!
የቤት ልጅ በገዛ ሰርጓ
ሳይታይ ወጓ፣ መዓረጓ
ለግርደና መዳረጓ!



በዚያች ቀን፣ በሰርጓ ዕለት
ከማአድ-ቤት አልወጣቻት
እኽልም አልቀመሰቻት
በርበሬ ሲወጠውጡ
ጌሾውን ሲወቃቅጡ
ምጣዱ፣ ድስቱ፣ ምን ቅጡ!
ሽንኩርቱን ስትልጥ ውላ…
ስጋውን ስትከትፍ ውላ…
ቁሌቱንም ስታቁላላ
ምጣዱን በጎን አስርራ
ስትጋግር፣ ወጥ ስትሠራ
አንጀቷን እያሳረረት
ደጋግመው እየጠራሯት
“አንቺዬ፣ አድራለሁ ቆሜ!”
ሲሉ አርሷ፤ “ለጌታዬ ዕድሜ!”
እያለች፤ “ለሚቴ ዕድሜ!”
ይኸውና ቀኑን ሙሉ
ዋለችው፣ መዋል አይበሉ!
ነገሩ ምርር ቢላት
ራስ ምታት ቢለቅባት
ከእንግዴህስ ቢጠሯት
ቢናገሯት፣ ቢሠሯት
የሆነው እስኪሆን ድረስ
ወሰነች ላለመመለስ።
የመጣው ይመጣል እንጅ
ምርር ያላት የቤት ልጅ
ነገሩ ሲላት እጅ-እጅ፤
“ማልሲ ኢኔ ኢሳጣል ቢለሽ
ኢዛው ላይ ጋቲሮ ኢደርሽ”
እያለች ከቤት ኮብልላ
ጠፋችው ሙሽሯን ጥላ!
የጥንቱ የአበው ተረት፤
“ጆሮ ደግፍ ላይ ዕንቅርት
በሰው ቁስልም ዕንጬት
አሹለህ ስደድበት!”
የሚሉት አለ መዓት…
ስለዚህ ባለችበት
በፀሎት፣ በመዋስእት
እግዚ’ሔር መጥኔ ይስጣት
እያልን እንለያት።

ገ/ኢ. ጐርፉ።